በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም፣ ክትትል እና ቁጥጥር ላይ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

)05

ባ

ማውጫ

ክፍል አንድ

መግቢያ.. 1

የፋይናንስ ምንጭ.. 2

የአሠራር መግለጫና ሚና (System description and roles) 3

የመንግሥት መ/ቤቶች ስልጣን.. 4

የኦዲቱ ዓላማ.. 4

የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫ.. 5

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት.. 6

ክፍል ሁለት

የኦዲቱ ግኝቶች.. 7

የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ለነዳጅ ግዥና አስተዳደር ሥራተገቢውን ትኩረት በመስጠት ጥናት ማድረጋቸውንናሥልጠና መስጠታቸውን በተመለከተ.. 7

ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓትመዘርጋቱን በተመለከተ.... 8

በፌዴራል መንግሥት ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች በእቅድ የተያዘው የነዳጅ በጀት ከአፈፃፀሙ ጋር መጣጣሙን በተመለከተ.. 9

በጋራ አገልግሎት ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በቅንጅት መጠቀምን ተመለከተ.. 12

ለመንግሥት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ ዕደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንፃር ተገምግሞ በኮታ የሚወሰን መሆኑን በተመለከተ.. 13

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽን በተመለከተ.. 15

በተለያየ ሞዴል ያላቸው ተሽከርካሪዎችን በአንድ ሊትር ነዳጅ የሚጓዙት ኪሎ ሜትር መጠን በተመለከተ.. 17

ጌጃቸው /የኪሎ ሜትር ቆጣሪ/ ለማይሠሩ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋላቸው መሆኑን በተመለከተ.. 18

ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር ሪፖርት መዘጋጅቱን እና መቅረቡን ተመለከተ.. 20

የነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥርን አስመልክቶ ችግሮችን በመለየት የማስተከከያ እርምጃ እንዲወሰድ መደረጉን በተመለከተ.. 21

የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለተ ወጥ/standardized/ እና ወቅታዊ የሆነ መመሪያ መኖሩን፣ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች መዘጋጀታቸውን እና ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን በተመለከተ.. 23

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቀቀም ላይ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን በተመለከተ............ 24

ክፍል ሶስት

የመደምደሚያ ሀሣቦች.. 26

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሣቦች 30

አባሪ 1:- የአሠራር መግለጫና ሚና (System description and roles)

2 :-የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. የአገሪቱን ኢኮኖሚ ግንባታ በማቀላጠፍ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለውን የትራንስፖርት አገልግሎት በይበልጥ ለማሻሻል ተሽከርካሪ የሚጠቀመውን ነዳጅ ከአገሪቱ አቅምና ፍላጎት ጋር የተገናዘበ መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም ነዳጅ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠን እና አስፈላጊ የሆኑ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡

2. የኢትዮጵያ መንግስት ወደ አገር ውስጥ ከሚያስገባቸው የተለያዩ ምርቶች ውስጥ ነዳጅ ከፍተኛ ድርሻ የሚይዝ እና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚያወጣ መሆኑ መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ2009/10 ወይም በ2002 በጀት ዓመት በጠቅላላውብር 16,826 ሚሊዮን የሚያወጣ 1,994.2 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶንስ ነዳጅ (ፔትሮሊዬም) በኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት አማካኝነት ወደ አገር ውስጥ ገብቷል፡፡ በአለም አቀፍ የገበያ ዋጋ መናር ምክንያት ከ2008/9 ወይም 2001 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ31.6 በመቶ ጭማሪ የሚያሳይ መሆኑን የብሄራዊ ባንክ አመታዊ ሪፖርት ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በ2003 በጀት ዓመት የነዳጅ ምርትን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት 1.7 ቢሊዮን ዶላር ወጪ እንደተደረገ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

3. ለፌዴራል መንግስት በ2002 በ.ዓ. ከተመደበው አጠቃላይ በጀት ውስጥ ከስድሳ እስከ ሰባ በመቶ (ከ60% እስከ 70%) ያህሉ ለተለያዩ ንብረቶች እና አገልግሎቶች ግዥ ወጪ እንደሚውል የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለመንግስታዊ ሥራዎች ለማስፈጸም የትራንስፖርት አገልግሎት ለማከናወን ለነዳጅ ግዥ የሚውለው ድርሻው ከፍተኛ ነው፡፡ ለአብነት ያህልም በ2002 በጀት ዓመት ብር 444,632,802.74፣ በ2003 በጀት ዓመት ብር 651,765,752.71 ያህል ወጪ እንደተደረገ ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ስለዚህ አገሪቱ ያላትን ውስን ሃብት ከፍተኛው ከውጭ አገር በሚገባ ምርት ላይ የምታውል በመሆኑ እና

ይህንንም በቁጠባ፣ በቅልጥፍና እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

4. የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 የተቋቋመ ሲሆን ኤጀንሲው በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን የግዥና ንብረት አስተዳደር ክንውንን ክትትል የማድረግ እና ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ለመንግስት ጉዳይ ማስፈጸሚያ ለትራንስፖርት አገልግሎት ማከናወኛ ለሚውል በመንግስት የተመደበላቸውን የነዳጅ በጀት በወጣለት እቅድ መሠረት በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እያከናወኑ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ በመሆኑም ይህን ከመንግስት በጀት ትልቅ ድርሻ ያለውን እና ለመንግስት ሥራ ማከናወኛ ወሳኝ ግብዓት የሆነውን /ነዳጅን/ እያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት ኢኮኖሚያዊ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችል ስርዓት የተዘረጋለት መሆኑን፣ የመንግስት የግዥ መመሪያን ተከትሎ ግዥ ማከናወኑን፣ በመንግስት የተሽከርካሪ ሥምሪት አጠቃቀም እና ጥገና መሠረት የተገለጹ አሠራሮችን ጠብቆ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ እየዋለ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

<u>የፋይናንስ ምንጭ</u>

5. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ለነዳጅ አገልግሎት የሚያውሉት ወጪ የፋይናንስ ምንጩ በዋንኛነት ከመንግሥት ከሚመደብ በጀት ሲሆን፣ በ2002 እና በ2003 በጀት ዓመታት በቅደም ተከተሉ ብር 470,271,383.58 እና ብር 667,192,485.69 የነዳጅ በጀት ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የተመደበላቸው ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ2002 በጀት ዓመት ብር 444,632,802.74 እና በ2003 ብር 651,765,752.71 ሥራ ላይ የዋለ መሆኑ ከመንግስት አመታዊ ሂሳብ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የመንግስት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓት ዓላማ

6. የተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት ዋና አላማ ለመንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የሚመደበውን የነዳጅ በጀት በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ወጥ የሆነ መመሪያ እንዲዘጋጅ በመርዳት ሀገሪቷ ለነዳጅ የምታወጣውን ወጪ በመቀነስ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በመጠቀም ይህ ከፍተኛ መዋለ ንዋይ የሚፈስበት ሀብት በአግባቡ ለታቀደለትና ለታለመለት አላማ እንዲውል ማድረግ ነው፡፡

የአሠራር መግለጫና ሚና (System description and roles)

7. የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ማለት የንብረት አጠቃቀም እና አወጋገድ ላይ የመተግበር እና ውሳኔ የመስጠት ሂደት ነው፡፡ በመንግሥት ንብረት መመሪያ ቁጥር 6/1991 መሠረት የመንግሥት ንብረት ማለት የመንግስትን ገንዘብ እና መሬት ሳይጨምር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ባለቤትነት ስር ያለ/በዚህ መመሪያ ቋሚ ንብረትና ስቶክ በሚል በሁለት የተከፈለው/ ንብረት ነው፡፡ ይህ መመሪያ ትርጓሜ በመንግሥት ባለቤትነት ሥር በሚገኙ ላይ ብቻ ሳይሆን በትውስት ወይም በሌላ ምክንያት በመንግሥት መ/ቤቶች የጥበቃ ኃላፊነት ሥር ለሚገኙት ንብረቶች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡የአሰራር ስርዓቱ ዝርዝር መግለጫው በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡ በተጨማሪም በዚህ መመሪያ ተሽከርካሪ እና ነዳጅ ከስቶክ እንደሚመደቡ ይገልፃል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ላይ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን አያያዝ፣ስምሪት እና አጠቃቀም የሚወስን መመሪያ እንዲሁም ከመንግስት ተሽከርካሪዎች ምዝገባ ፣አያያዝ ፣ስምሪት እና አጠቃቀም ጋር በተገናኘ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚገባቸው ቅጾች የተዘጋጁ መሆኑ ታውቋል፡፡

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሥልጣን

8. በአዋጅ ቁጥር 647/2001 አንቀጽ 4 የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፡፡

   1. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ግምጃ ቤት (Treasury) የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ጥያቄ ሲያቀርቡ ከፌዴራል መንግሥት ገቢዎች እና ሌሎች ፈንዶች ለሥራ ማስኬጃ የሚሆን በተገቢው መንገድ ወጪ አድርጎ የማከፋፈል ሥራ መሥራት፣
   2. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችም የተመደበላቸውን በጀት ለዋና ክፍል፣ ለንዑስ ክፍል፣ ለፕሮጀክት ወይም ለፕሮግራም የተጠቀሙበትን በጀት ወይም ተጨማሪ ብድር ወይም እርዳታ በቁስም ሆነ በጥሬ ገንዘብ ከሀገር ውስጥም ይሁን ከውጭ የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፡፡

9. እንዲሁም በፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ላይ የሚከተሉት ተግባር እና ሃላፊነት ተሠጥቷቸዋል፡፡

   1. የተሽከርካሪዎችን የኪ.ሜ. ቆጣሪ (ጌጅ) የተሟላ ና በትክክል መስራቱን በመከታተል ማረጋገጥ ፣
   2. የእያንዳንዱን ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታ መጠን ከሸፈነው ኪ.ሜ. መጠን ጋር በመመዝገብ ሪፖርት በየወሩ ማቅረብ፣
   3. እንዲሁም ለመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሚውለው ነዳጅ ከውጤት ጋር በተገናዘበ መልኩ ስለሚሰራጭበት መንገድ ተጨማሪ ዝርዝር የውስጥ አሠራርና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት፣በየወሩም ሪፖርት እንዲያቀርብ በማድረግ ተገቢውን የአፈጻጸም ግምገማ ማካሄድ፣ የሚሉት ናቸው፡፡

የኦዲቱ አላማ

10. የኦዲቱ ዋና ዓላማ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳድር ኤጀንሲ፣ የተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን እንዲሁም ይህንኑ ስርዓት መሰረት በማድረግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ተጨማሪ ዝርዝር የውስጥ አሰራር እና ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን፣ የተዘረጋውም ስርዓት ተፈጻሚ መሆኑን እና ነዳጅ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ይህንን በተመለከተ ያሉትን የአሰራር ችግሮች በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ኃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች

11. ከላይ በተገለጸው የኦዲት ዓላማ ሥር ሶስት ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነሱም፡-

1. የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን የግዥና ንብረት አስተዳደር (ነዳጅን) ክንውን ክትትል በማድረግ ሪፖርት ለገ/ኢ/ል/ ሚኒስትሩ ማቅረቡን እና ኦዲት ማድረጉን ማጣራት፣
2. ማንኛውም የፌዴራል መንግስት መ/ቤት ለተሽከርካሪዎች ስምሪት የሚያስፈልገውን የነዳጅ በጀት መጠን በእቅድ የያዘውን የመንግስትን ሥራ ለማስፈጸም በሚያስችል ጥናት ላይ የተመሰረተ እቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ መደረጉን ማጣራት፣
3. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን፣ በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ማጣራት፣

የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

12. በኦዲቱ በናሙና በተመረጡ 11 መ/ቤቶች በሶስት በጀት አመታት ውስጥ ማለትም ከ2002 እስከ 2004 ባለው ጊዜ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ወጥ የሆነ

የነዳጅ አጠቃቀም ስርዓት መኖሩን እና ተፈጻሚ መሆኑ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና በተጨማሪም ለኦዲት በናሙና በተመረጡ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፣ግብርና ሚኒስቴር፣ማዕድን ሚ/ር፣ ጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ ማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ ኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ዋናው መ/ቤት እና በደብረማርቆስ ዲስትሪክት፣ የማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እና በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሲሆን፣ ኦዲቱም የመ/ቤቶቹን የሚመለከታቸው የስራው ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በቼክ ሊስት በመወያየት እና በማጣራት፣ ለነዳጅ አፈጻጸም ስራ ላይ የዋሉ የተለያዩ ቅጾችን እና ዶክመንቶችን በመከለስ እና አሰራሩን በአካል ተገኝቶ በማየት ነው፡፡

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት

13. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሶስት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 27 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (evaluative criteria) የተዘጋጁ ሲሆን፣ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የመንግሥትና ሕዝባዊ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ግዥ ሥምሪት አጠቃቀምና ጥገና መመሪያ፣ የስቶክ ማኔጅመንት መመሪያ፣ የፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ፣ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የተካሄደ ጥናት ሪፖርት፣ የመኪና አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ እና ቃለ መጠይቆች ናቸው፡፡ በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አስተያየት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲቱ ግኝቶች

የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ለነዳጅ ግዥና አስተደደር ሥራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ጥናት ማድረጋቸውን እና ሥልጠና መሠጠቱን በተመለከተ፤

14. የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ለነዳጅ ግዥና አስተደደር ሥራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ስለ መንግሥት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል ጥናት ሊያካሂዱ እንደሚገባ የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ይገልጻል፡፡

15. በኦዲቱ ተመርጠው ከታዩ 11 መ/ቤቶች በ 9ኙ (በግዥና ንብረት አስተዳደር፣ በግብርና ሚ/ር፣ በማዕድን ሚኒስቴር፣ በግብርና ምርምር ኢንሲቲትዩት፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እናበኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ደብረማርቆስ ዲስትሪክት) የበላይ ኃላፊዎች ነዳጅን በአግባቡ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል ጥናት እንዲካሄድ እና ሥልጠና እንዲሰጥ የማድረግ ሥራ አላከናወኑም፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ሁለቱ ደግሞ በግብርና ሚ/ር በ1997 ዓ.ም. በመ/ቤቱ የተዘጋጀ የተሽከርካሪ አጠቃቀም መመሪያ መኖሩን እና እየተጠቀሙበት መሆኑን ቢገልጹም ወቅታዊ በማድረግ እየተጠቀሙበት አለመሆኑን እና በማዕድን ሚ/ር መ/ቤት ለውስጥ አሰራር እንዲያመች በመመሪያ ደረጃ ተዘጋጅቶና በበላይ አመራሩ በወቅቱ የጸደቀውን ሠነድ መነሻ በማድረግ እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ ነገር ግን የሌሎችን መ/ቤቶች ልምድ በመውሰድ የተዘጋጀ ጥናታዊ ሠነድ እንደሌለ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

16. እነዚህ ጥናቱን ካላካሄዱት ውስጥ ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ ጥናት እንዲካሄድ የሚገልጽ መመሪያ አለመኖሩን፤ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቂ የቴክኒክ ሙያ ያለው ሰራተኛ አለመኖሩን እና የቴክኒክ ባለሙያ ለመቅጠር በተደጋጋሚ ማስታወቂያ የወጣ ቢሆንም ማግኘት አለመቻሉን፤በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተቀመጠው አደረጃጀት በአዲስ መልክ የተዋቀረ መሆኑን እና በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ደብረማርቆስ ዲስትሪክት ጥናት የሚደረገው በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት በመሆኑ፣ በዲስትሪክት ደረጃ ቢጠና ተግባራዊ ለማድረግ የቦርድን ውሳኔ የሚጠይቅ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

17. እንዲሁም ስለሁኔታው የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ኃላፊዎች ተጠይቀው የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትን ለመዘርጋት ዝርዝር ጥናት የሚጠይቅ በመሆኑ በ2005 በጀት ዓመት ዕቅድ ውስጥ እንዲካተት መደረጉን ገልጸዋል፡፡

18. በኦዲቱ ወቅት እንደተገነዘብነው የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ለነዳጅ ግዥና አስተደደር ሥራ ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠታቸው ሥራው በአግባቡ የማይከናወን መሆኑን ነው፡፡

ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

19. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ነዳጅን እንዲጠቀሙ የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

20. በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የወጣ የተሽከርካሪ ጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት እስከ 2004 በጀት ዓመት መጨረሻ አንዳልነበረ ታውቋል፡፡ በመሆኑም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩት 11 መ/ቤቶች በ10ሩ መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች ጥገና እና የእንክብካቤ ሥርዓት ያልተዘረጋላቸው መሆኑ፣ እንዲሁም በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የግል ማህደራቸው ከታዩት ተሽከርካሪዎች ከ2002 ዓ.ም. በፊት የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓትን የሚያመለክት

እና የተሸከርካሪዎችን ሁኔታ የሚገልጽ መረጃዎች የነበሩ ቢሆንም፣ ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ግን መረጃዎችን ማግኘት አልተቻለም፡፡

21. ስለ ሁኔታው በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በተሽከርካሪዎች የግል ማህደር ውስጥ እስከ ግንቦት 2002 ዓ.ም ድረስ መረጃዎች እንደነበሩ የገለጹ ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ ላሉት ሁኔታዎች ግን ለምን እንደሌሉ መልስ አልሰጡም፡፡

22. እንዲሁም የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በ2004 በ.ዓ. መጨረሻ የፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 በኤጀንሲው ወጥቶ ለአስፈጻሚዎች የተሰራጨ በመሆኑ ችግሩ ሊቃለል እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

23. በፌደራል መንግሰት መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መውጣቱ ተገቢ እና አስፈላጊ ቢሆንም ከዚህ በፊት ወጥ የሆነ የተሽከርካሪ ጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት አለመዘርጋቱ እና በተሽከርካሪ የግል ማህደር ውስጥ የተሽከርካሪውን የህይወት ታሪክ እና የወጣውን የነዳጅ ፍጆታ እስከ 2004 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ያለውን የሚያመለክት መረጃ አለመኖሩ አሁን የወጣውን መመሪያ ተግባራዊ ማድረግን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች በእቅድ የተያዘው የነዳጅ በጀት ከአፈፃፀሙ ጋር መጣጣሙን በተመለከተ፤

24. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚመደበው በጀት በዓመቱ የታቀደውን የመንግሥት ሥራ ለማከናወን በሚያስችል መልኩ በጥናት ላይ መመሥረት እና አፈጻጸሙም በጀቱን በእቅዱ መሠረት በሚገባ መጠቀማቸውን የሚያመለክት ሊሆን ይገባል፡፡

25. ከ2002 እስከ 2003 ዓ.ም ባለው የበጀት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ 10 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በአራቱ (በ4) የነዳጅ በጀት (በሂሳብ መደብ 6217) ከአፈጻጸሙ ጋር ሲታይ የማይጣጣም ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሶስቱ ከ15% በላይ በጀቱን ሳይጠቀሙና አንድ መ/ቤት ደግሞ ከበጀት በላይ ወጪ አድርገው

ተገኝተዋል፡፡ እነርሱም - በማዕድን ሚ/ር በ2002 ዓ.ም. (18.25%) እና 2003 ዓ.ም. (24.45%)፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2002 በ.ዓ. (15.12%) እንዲሁም በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን በደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት በ2003 ዓ.ም. (38.69%) ከተያዘላቸው ከበጀት በታች ተጠቅመው ተገኝተዋል፡፡ እንዲሁም በጤና ጥበቃ ሚ/ር በ2002 ዓ.ም. የመንግስት የበጀት አዋጅ መመሪያ ሳይከተል ብር 62,350.8 (7.68%) ከተያዘለት በጀት በላይ ተጠቅሟል፡፡ ዝርዝሩ በሚከተለው <u>ሠንጠረዥ 1</u> ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 1

26. በናሙና በተመረጡ መ/ቤቶች የየበጀት ዓመቱ የነዳጅ በጀት አፈጻጸም ዝርዝር መግለጫ፣

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	በሂሣብ መደብ 6217 ለነዳጅ የተመደበ በጀት 2002 ዓ.ም.	አፈጻጸም 2002 ዓ.ም.	ልዩነት		በሂሣብ መደብ በ6217 ለነዳጅ የተመደበ በጀት 2003 ዓ.ም.	አፈጻጸም 2003 ዓ.ም.	ልዩነት	
				በማነስ	በመብለጥ			በማነስ	በመብለጥ
1	የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ (አዲስ በመሆኑ)	18,800	300	18,500 (98%)	--	163,178	152,639.25	10,538.75 (6.5%)	--
2	ማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ	4262000.	3967296.42	294703.58 (6.9%)		4,292,000	3,682,314.82	609,685.68 (14.2%)	
3	የማዕድን ሚ/ር	601,806	491,936.09	109,869.91 (18.2%)	--	700,000	528,830.91	171,169.09 (24%)	--
4	ባህርዳር ዩኒቨርስቲ	3,936,300	3,341,191.80	595,108.2 (15.1%)		5,567,000	5,463,050	103,950 (1.8%)	--
5	በመንገዶች ኮርፖሬሽን ደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት	8,298,820.97	7,813,532.54	485288.45 (5.2%)	--	18,357,967.5	11,255,803.	7,102,163.56 (38.68%)	--
6	የጤና ጥበቃ ሚ/ር	811,600	873,950.80	--	62,,350.80 (7.6%)	1,608,174.19	1,596,229.36	11,944.83 (0.7%)	--

27. ስለ ሁኔታው በናሙና የተመረጡት የእነዚሁ መ/ቤቶች ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የእያንዳንዱ በጀት ዓመት በጀት ሲያዝ ከዚህ በፊት በነበረው በጀት ላይ በመመርኮዝ እንጂ በጥናት የተደገፈ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

28. ስለሆነም የእያንዳንዱን ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታ በመለካት ከመ/ቤቱ የሥራ ስፋት ጋር በማነጻጸር ለነዳጅ የሚታቀደው በጀት በጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ የሚመደበው የነዳጅ በጀት አጠቃቀም ከስራው ስፋትና መጠን ጋር እንደማይጣጣምና በጀቱ ለብክነት እና አለአግባብ ሥራ ላይ እንዲውል ምቹ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል፡፡

በፌዴራል መ/ቤቶች በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በቅንጅት መጠቀምን በተመለከተ፤

29. በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች የየሥራ ክፍሎችን የተሽከርካሪ ጥያቄዎች በማገናዘብ እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙትን የመ/ቤቱ ሠራተኞች በማቀናጀት ለሥራ በጋራ በመጠቀም ነዳጅን በቁጠባ መጠቀም እንደሚገባ የመንግሥትና ህዝባዊ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ግዥ ሥምሪት አጠቃቀምና ጥገና መመሪያ ይገልጻል፡፡

30. ሆኖም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ከ11 መ/ቤቶች በ8ቱ በጋራ አገልግሎት ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙ ሰራተኞችን በጋራ ተቀናጅተው ለሥራ የተሠማሩ እና የተጓጓዙ ስለመሆኑ ማስረጃ ተጠይቀው ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡

31. እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት በታዩ በማዕድን ሚ/ር ከ2002- 2003 በ.ዓ. ያለውን የስምሪት ሰነድ ሙሉ በሙሉ አልተገኘም፤ በግብርና ምርምር ማዕከል የጋራ ጉዞን የሚገልጽ መረጃ በስምሪት ክፍሉ እንደ ሥራው አመቺነት የሚከናወን ቢሆንም በአንዱ የጉዞ ጠያቂ ብቻ እየተመዘገበ የሚፈጸም በመሆኑና ቅጹም በሁለት ኮፒ ተሰርቶ አንዱ በመረጃነት እንዲቀመጥ የተደረገበት ሁኔታ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም በማዕከላዊ እስታትስቲክስ በባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሙሉ በሙሉ የስምሪት ሰነድ መረጃውን ማግኘት አልተቻለም፡፡

32. ስለሁኔታው በናሙና ከታዩት መ/ቤቶች የማዕድን ሚ/ር የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በስምሪት ክፍሉ የሰው ሃይል እጥረት እና ከሥራ መደራረብ የተነሳ የታየ የመረጃ አያያዝ ክፍተት ስለሆነ ወደፊት ተጠናቅሮ እንደሚሰራበት እና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የጋራ ጉዞን የሚያመለክት መረጃ ባይኖርም አቀናጅተው እንደሚያሰማሩ ገልጸዋል፡፡

33. በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን የየሥራ ክፍሎችን የተሽከርካሪ ጥያቄዎች በማገናዘብ እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙትን የመ/ቤቱን ሠራተኞች በማቀናጀት ለሥራ በጋራ እንዲጠቀሙ አለማድረግ ለመንግስት መ/ቤቶች የሚመደበውን ነዳጅ በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዳይጠቀሙ ያደርጋል፡፡

ለመንግስት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ ዕደላ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ የሚወሰን መሆኑን በተመለከተ፤

34. ለመንግስት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ ዕደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ መወሰን አለበት፡፡ እንዲሁም ለመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታ የከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት መመሪያ መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

35. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 11 መ/ቤቶች በ8ቱ ነዳጅን ለመቆጣጠር የሚያስችል በሳምንትም ሆነ በወር ለአንድ ተሽከርካሪ የተመደበ የነዳጅ መጠን የሚገልጽ ሰነድ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡ ዝርዝር ሁኔታው በሚቀጥለው ሰንጠረዥ 2 እና በማብራሪያው_ ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 2

36. **በከተማ ውስጥ ለሥራ ተሠማርተው በወርም ሆነ በሳምንት የነዳጅ ኮታ መጠን ያልተመደበላቸው ተሽከርካሪዎች ዝርዝር**

ተ.ቁ	የተቋሙ ሥም	የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር	የተቀዳው የነዳጅ መጠን በሊትር	ነዳጁን የተጠቀመበት ቀናት ብዛት	በአንድ ቀን የተጠቀመው አማካይ ሥሌት በሊትር
1	ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	4-12463	600	11	54.5
		4-15058	170	2	85
2	ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ	4-10755	951.23	22	43.24
		4-09583	180	4	45
3	ማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ	4-11158	156.69	1	156.69
		4-11158	340	10	34
4	ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት	4-02175	360	19	19
		4-01915	130	4	32.5
5	ማዕድን ሚ/ር	4-08937	130	6	21.67
		4-03498	135	8	16.87

ከላይ በሰንጠረገዡ ላይ እንደተመለከተው ነዳጅ ያለገደብ /ኮታ/ እንደተቀዳላቸው በሥራ ላይ ከዋሉ የነዳጅ፣ ቅባት እና ዘይት መጠየቂያ ቅጾች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

37. እንዲሁም በግብርና ሚ/ር የነዳጅ ኮታ መኖሩ የተገለጸ ቢሆንም፣ በወር የተወሰነው ኮታ ከ120-160 መሆኑ የግብርና ሚ/ር ከተሽከርካሪ አጠቃቀም መመሪያ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ ሰሌዳ ቁ.4-14079 በ26 ቀን ውስጥ 510 ሊትር እና 4-00617 በ14 ቀናት ውስጥ 150 ሊትር ነዳጅ መቅዳታቸውን ከነዳጅ፣ ቅባት እና ዘይት መመዝገቢያ ቅጽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

38. ስለሁኔታው የማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ከመ/ቤታቸው የሥራ ባህሪ አንጻር ሊሞላ እንደሚችል ቢገምቱም በወቅቱ ስላልነበሩ አሁን ላይ ሆነው መናገር የማይችሉ መሆኑን ገልጸዋል፤ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በቀን በከተማ ውስጥ ለግዥ እና ለሌሎች ሥራዎች ከፍተኛ የተሽከርካሪ ምልልስ በመኖሩ መሆኑን ሲገልፁ የግብርና ሚ/ር

ደግሞ ተሽከርካሪዎች ለመ/ቤቱ ሰራተኞች ጧት እና ማታ ሰርቪስ የሚሰጡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

39. እንደዚሁም ለመንግስት የበላይ ኃላፊዎች በወር የተመደበ የነዳጅ መጠን ናፍጣ እስከ 165 ሊትር እና ቤንዚን 135 ሊትር እንደሆነ የከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች ለመወሰን ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በ17/3/1997 በቁጥር ጠ80. አጠ3/101/02 በተጻፈው የሚኒስትሮች ም/ቤት መመሪያ ያመለክታል፡፡

40. በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በግንቦት ወር 2004 ዓ.ም. ለሰሌዳ ቁጥር 4-14152 ለፕሬዝዳንቱ ተሽከርካሪ 450 ሊትር ነዳጅ እንዲሁም ለሰሌዳ ቁጥር 4-13617 ለምክትል ፕሬዝዳንቱ ተሽከርካሪ 300 ሊትር ነዳጅ ለመንግስት የበላይ ኃላፊዎች በመመሪያው ከተፈቀደው ውጭ የተቀዳላቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በሥራ ላይ ከዋለ ከነዳጅ፣ ቅባት እና ዘይት መመዝገቢያ ቅጽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

41. ስለሁኔታው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የኃላፊዎች ተሽከርካሪዎች በመሆናቸው ለስብሰባ ብዙ ቦታ ስለሚሄዱ የተሰጠ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

42. ለመንግስት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ ዕደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ አለመወሰኑ፣ በፌደራል መንግስት ተሽከርካሪ የነዳጅ አጠቃቀም የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡

<u>በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ ስለመኖሩ በተመለከተ፤</u>

43. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ለቁጥጥር እና ክትትል ያመች ዘንድ ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ ሊኖር እና በሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡

44. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት 11 መ/ቤቶች በሁሉም የተለያዩ ቅጾች ፎርማት ቢያዘጋጁም ወጥ በሆነና ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ነዳጅ ሲቀዳ የኪሎ ሜትር ንባብ፣ ተሽከርካሪው ሲሰማራ የሄደበት እና የሚመለስበት ሰዓት በተዘጋጁት ቅጾች ላይ የማይመዘገብ መሆኑን ሥራ ላይ ከዋሉ የነዳጅ መመዝገቢያ ቅጾች ላይ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ዝርዝር ሁኔታውም፡-

45. በጤና ጥበቃ ሚ/ር በኦዲቱ ወቅት መረጃዎች ተከልሰው በመስክ ስምሪት ከታዩ ከ03/10/2003 -12/08/2004 ዓ.ም ከታዩ 380/100%/ የስምሪት ቅጾች እና በአዲስ አበባ በጋራ አገልግሎት ከታዩት ከ02/08/2004 -02/09/2004 ዓ.ም 493 /100%/ የስምሪት ሰነዶች ላይ የኪሎ ሜትር ልዩነት የማይመዘገብ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በአቢሲኒያ ካርድ ነዳጅ መጠየቂያና መቀበያ ፎርም ላይ የነዳጅ አይነት፣ የሚሄደው ኪሎ ሜትር፣ የመነሻ ኪሎ ሜትር፣ ካርዱ ላይ የተጫነበት የብር መጠን፣ ከካርዱ የተጠቀመው የነዳጅ መጠን በሊትር፣ የቀረው የነዳጅ መጠን እና በዕለቱ የሚያስፈልገው የነዳጅ መጠን ፎርማቱ የሚጠይቅ ቢሆንም ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡

46. በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በ2002 እና 2003 ዓ.ም የተሽከርካሪ የከተማ ውስጥ እና የመስክ ስምሪት መመዝገቢያና መቆጣጠሪያ ቅጽ ላይ ጉዞ ሲጀምር እና ጉዞ ሲፈጽም የኪሎ ሜትር ንባብ ልዩነት እና የገንዘብ ወጪ /የነዳጅና የቅባት/ የማይገለጽ መሆኑ ታውቋል፡፡

47. እንደዚሁም በኦዲቱ ከታዩ ከ11 መ/ቤቶች በ9ኙ በመንግሥትና ህዝባዊ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ግዥ ሥምሪት አጠቃቀምና ጥገና መመሪያ መሰረት ዕለታዊ የመንግስት መ/ቤቶች ስምሪት ቅጽ በሁለት ኮፒ መዘጋጀት ሲገባው በአንድ ኮፒ የሚዘጋጅ፣ በመረጃነት ተጠናቅሮ የማይያዝ እና ተሽከርካሪው የወጣበት እና የሚመለስበት ሰዓት እንደማይመዘገብ ከዕለታዊ ሥምሪት ቅጽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

48. እነዚሁ መ/ቤቶች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የአሰራር ሥርዓቱ ያለና የተዘረጋ ቢሆንም፣ በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ እና እነዚህን ችግሮች በቅርቡ የመከታተልና የማስፈጸም አቅም በመላላቱ የተከሰተ ሁኔታ እንጂ አስፈላጊነቱ የማያጠያይቅ ሆኖ መታረም ያለበት አሰራር መሆኑን፤ የጤና ጥበቃ ሚ/ር አልፎ አልፎ በሥራ መደራረብ ምክንያት የተፈጠረ ችግር መሆኑን እና በቀጣይ የማስተካከያ እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን እና የማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ አልፎ አልፎ ከሥራ ብዛት የተነሳ ሳይሞሉ እንደቀሩ እና አሁን የተገነዘቡ መሆኑን እና በቀጣይ ክፍተቱን ለመሙላት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

49. እያንዳንዱ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት በመመሪያው መሠረት ወጥ የነዳጅ መመዝገቢያ ቅጽን አለማዘጋጀት እና የሚፈለጉ መረጃዎችን በአግባቡ

አለመመዝገብ የነዳጅ ቁጥጥሩን እና ክትትሉን በማዳከም ነዳጅ ለብክነት እንዲዳረግ ያደርጋል፡፡

የተለያየ ሞዴል ያላቸው ተሽከርካሪዎችን በአንድ ሊትር ነዳጅ የሚጓዙትን ኪሎ ሜትር መጠን በተመለከተ፤

50. እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነት፣ በሞዴልና በአገለገለው ዕድሜ መጠን ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል መታወቅ እና በዚሁ መሠረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

51. በናሙና ተመርጠው ኦዲት ከተደረጉ 11 መ/ቤቶች በ7ቱ፣ በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ በግብርና ምርምር ኢንስትቱዩት፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ደብረማርቆስ ዲስትሪክት እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነትና በሞዴል ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል የሚገልጽ ሰነድ አለማዘጋጀታቸው እና ተግባራዊ አለማድረጋቸው ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩም

52. በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በሞዴልና በአይነት ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ ምን ያህል ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል የሚገልጽ መመሪያ ወይም ሰነድ በዩኒቨርሲቲው በ2002 ዓ.ም የተዘጋጀ የተገኘ ቢሆንም፣ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤ በጤና ጥበቃ ሚ/ር ሁለት ተሽከርካሪዎች የሰሌዳ ቁጥራቸው 4-15332 እና 4-15335 ብቻ በአንድ ሊትር 6.5 ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችሉ የታወቀ ሲሆን፣ መ/ቤቱ በዓይነት እና በሞዴል ለይቶ በቀሪዎቹ 99 ተሽከርካሪዎች ልኬት ያልተከናወነላቸው መሆኑ፤ በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት ለከባድ ተሽከርካሪዎች 1.43 በሊትር፣ ለትናንሽ ደግሞ 5.88 በሊትር ተብሎ የተቀመጠ ቢሆንም፣ በአይነትና በሞዴል ያልተለዩ መሆናቸው እና በማዕድን ሚ/ር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በሞዴልና በአይነት ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ ምን ያህል ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል የሚገልጽ ሰነድ ከ5 ዓመት በፊት የተዘጋጀ ቢሆንም፣ ወቅታዊ

ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት በቃለ መጠይቅ ከተሰጠው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

53. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባህር ዳር ቅርንጫፍ መ/ቤት በተለምዶ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ዋናው መ/ቤት እና በሌሎች የእስታትስቲክስ ጽ/ቤቶች በአማካይ አንድ የመ/ቤቱ ተሽከርካሪ በሊትር ከ6 ኪሎ ሜትር በላይ ይጓዛል በሚለው እሳቤ 6.5 እና 7ኪሎ ሜትር በሊትር እንደሚጠቀሙ፤ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሰነድነት ባይኖርም፣ እያንዳንዱን ሞዴል በሙከራ (ፓይለት) ዘዴ በመለካት እንደሚጠቀሙ እና በአሁኑ ጊዜ ግን ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ኮሚቴ ተዋቅሮ ጥናት በመደረግ ላይ መሆኑን፤ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ ከዚህ በፊት በኪሎ ሜትር ካርድ ላይ ተሰልቶ ከሚታወቅ ውጭ በሰነድ መልክ በዝርዝር መረጃ የመያዝም ሆነ የማደራጀት ልምድ እንደሌለ እና አሁን ግን መረጃ አሰባስቦ ለማደራጀት የሚሞከር ጅምር ስራ መኖሩን፤በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አንድ ተሽከርካሪ በሞዴልና በአይነት በአንድ ሊትር ይህን ያህል ይጓዛል በሚል በመመሪያ ማስቀመጡ በአሰራር ላይ ያስቸግራል የሚል ስጋት መኖሩን፤ በግብርና ሚ/ር ተሽከርካሪዎቹን በዓይነትና በሞዴል በአንድ ሊትር ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል በነዳጅ መቆጣጠሪያ ቅጽ አማካዩን ወስደው እንደሚሰሩ እና ወደፊት ኮሚቴ በመመስረት የነዳጅ ፍጆታ በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር የሚለው እቅድ መያዙን እንዲሁም በኢትዮጵያ መንገዶች ኮርፖሬሽን ደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት ይህንን ለማከናወን በዲስትሪክት ደረጃ ባለሙያ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

54. እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነትና በሞዴል ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል አለመታወቁ እና በዚሁ መሠረት ተግባራዊ አለመደረጉ፣ ተሽከርካሪዎች የተጠቀሙትን ነዳጅና የተጓዙበትን ኪሎ ሜትር የሸፈነ ለመሆኑ ለማጣራት የሚያዳግት እና ነዳጅን በትክክል የተጠቀሙበት መሆኑን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ተገቢው የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት እንዳይኖር በማድረግ የነዳጅ በጀትን በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

ጌጃቸው (የኪሎ ሜትር ቆጣሪ) ለማይሠሩ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋላቸው መሆኑን በተመለከተ፤

55. የተሽከርካሪዎች ኪ/ሜትር ቆጣሪ /ጌጃቸው/ ለማይሠሩ የመንግሥት መ/ቤት ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ እና በዚሁ መሠረት ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

56. በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር 4-01922፣ 4-02769፣ 4-01921፣ 4-02768፣ 4-00720፣ 4-01750፣ 4-01924፣ 4-01917 ከስምሪት ክፍል በተገኘው መረጃ ጌጃቸው የሚሰራ መሆኑ ሲገለጽ፤ ነገር ግን በ2002 ዓ.ም በነዳጅና ቅባት መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

57. በናሙና ከተመረጡ 11 የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች በ10ሩ ጌጃቸው የማይሰሩ ተሽከርካሪዎች እንዲቆሙ ከማድረግ ወጪ የመቆጣጠሪያ ሥርዓት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡

58. በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጌጃቸው የማይሰሩ 6 ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ ሳይዘጋጅ በሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ፤ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ ጌጃቸው የማይሰሩ 2 ተሽከርካሪዎች በሥራ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ፤ በጤና ጥበቃ ሚ/ር ጌጃቸው የማይሰሩ 2 ተሽከርካሪዎች በሥራ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ፤ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጌጃቸው የማይሰሩ 17 ተሽከርካሪዎች በሥራ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ፤በግብርና ሚ/ር ጌጃቸው የማይሰሩ 17 ተሽከርካሪዎች በሚ/ር መ/ቤቱ በሥራ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ እና በማዕድን ሚ/ር ጌጃቸው የማይሰሩ 7 ተሽከርካሪዎች በሚ/ር መ/ቤቱ በሥራ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ ተረጋግጧል፡፡

59. በናሙና ተመርጠው የታዩ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለወደፊት በታንከራቸው ላይ የሽቦ ወንፊት ለማሰራት እቅድ መያዙን፤ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጌጃቸውና ኪሎ ሜትራቸውን ለማሰራት መሞከሩን እና ዕቃው በገበያ ላይ ባለመገኘቱ ሊጠገኑ አለመቻላቸውን፤ የግብርና ሚ/ር አብዛኛውን ተሽከርካሪዎች ለከተማ ውስጥ ሥራና ለሰራተኞች ሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸውን እና ለወደፊት ኪሎ ሜትር ቆጣሪው ተገዝቶ እንዲገጠም ወይም የተሽከርካሪዎቹ ቆጣሪ

እስኪገጠም ከአገልግሎት ውጭ ለማድረግ እንደታሰበ እና የማዕድን ሚ/ር ጌጃቸው የማይሰሩ ሞዴላቸው የቆዩ ተሽከርካሪዎች ስለሆኑ ቆጣሪ ከገበያ ላይ መጥፋቱን ገልጸዋል፡፡

60. ጌጃቸው የማይሠሩ የመንግሥት መ/ቤት ተሽከርካሪዎች ተለይተው የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት አለመዘርጋቱ ለነዳጅ የሚመደበውን በጀት በአግባቡ ለታለመለት አላማ እንዳይውል በማድረግ ነዳጅ ለብክነት እንዲጋለጥ እገዛ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ተሽከርካሪው በተቀዳለት ነዳጅ ምን ያህል ኪ/ሜትር የተጓዘ መሆኑን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር ሪፖርት መዘጋጀቱን እና መቅረቡን በተመለከተ፤

61. የመንግሥትና ህዝባዊ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ግዥ ሥምሪት አጠቃቀምና ጥገና መመሪያ መሰረት በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

62. በናሙና ተመርጠው በኦዲት በታዩ 11 መ/ቤቶች በ8ቱ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየወሩ መጨረሻ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በቅጽ ላይ በመሙላት በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ተረጋግጧል፡፡

63. ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የእነዚሁ መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በማዕድን ሚ/ር በቀጣይ ጊዜያት ሪፖርቱ እንደሚዘጋጅና ለበላይ ኃላፊና ለተጠቃሚ ዳይሬክቶሬቶች እንዲደርስ እንደሚደረግ፤ በግብርና ሚ/ር ወደፊት ከሐምሌ 01/04 ጀምሮ እንደሚዘጋጅ፤ በግብርና ምርምር ማዕከል የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓቱ ያልተዘረጋ በመሆኑ እንጂ ጌጃቸው ለሚሰሩ ተሽከርካሪዎች ማዘጋጀትና ማቅረብ የሚቻል መሆኑን፤ በጤና ጥበቃ ሚ/ር ሥራው ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም፣ ተሽከርካሪዎች ለመስክ ሥራ ሲሰማሩ መረጃ ማግኘት

ባለመቻሉ መቋረጡን፤ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ መሆኑን፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ ለወደፊቱ እንደሚሻሻል እና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የፈጀው ነዳጅ መጠን እንደሚገለጽ ነገር ግን የሸፈነው ኪሎ ሜትር ወደፊት እንዲካተት እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

64. በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ በነዳጅ አጠቃቀም ላይ ቁጥጥር እና ክትትል ሥራ ላይ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ የተጠያቂነት ስርዓት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

የነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥርን አስመልክቶ ችግሮችን በመለየት እርምጃ እንዲወሰድ መደረጉን በተመለከተ፤

65. እያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት በነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥር የሚታዩ የተለያዩ ችግሮችን በመለየት ለችግሮቹ መፍትሄ በማፈላለግ በወቅቱ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

66. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ተመርጠው ከታዩ11 መ/ቤቶች በ8ቱ ከኮታ በላይ ሲጠቀሙ በነበሩ እና በኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ደብረማርቆስ ዲስትሪክት በ1 ሊትር ከወጣላቸው የኪ.ሜ. ልኬት በታች ያሽከረከሩ አሽከርካሪዎችን በመለየት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዝርዝር ሁኔታውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

67. በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሰሌዳ ቁጥር 4-15387 በ13/10/03 በቀን ሁለት ጊዜ /2X60/ በድምሩ 120 ሊትር/ እዛው በደብረ ማርቆስ ከተማ ውስጥ ተሰማርቶ ነዳጅ የተቀዳለት መሆኑ ታውቆ የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ አለመኖሩን፤ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ ሰሌዳ ቁጥር 4-15372 በ17/06/03 በቀን ሁለት ጊዜ /20 ሊትር እና 30ሊትር በድምሩ 50 ሊትር/ ነዳጅ የተቀዳለት መሆኑ ታውቆ የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ አለመኖሩን፤

68. በጤና ጥበቃ ሚ/ር ነዳጅ ለመቅዳት አንድ መኪና አንድ ካርድ ብቻ እንደሚፈቀድለት የሚታወቅ ሲሆን፣ ለሰሌዳ ቁጥር 4-02011 ግን በሁለት ካርድ

በካርድ ቁጥር 15939 እና በካርድ ቁጥር 9143 የተጠቀመ መሆኑ ተመዝግቦ ተገኝቶ የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር 4-02011 በካርድ ቁጥር 9143 በ01/07/09 እ.ኤ.አ. በአንድ ቀን ብቻ ሶስት ጊዜ ከሰንጋ ተራ ቶታል ነዳጅ ማደያ በድምሩ 269.98 ሊትር ነዳጅ በከተማ ውስጥ ለተንቀሳቀሰበት የተቀዳለት መሆኑ፣እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ በካርድ ቁጥር ቁጥር 9143 በ03/08/09 እ.ኤ.አ. በአንድ ቀን ብቻ 4 ጊዜ ከሰንጋ ተራ ቶታል ነዳጅ ማደያ በድምሩ 323.14 ሊትር ነዳጅ የተቀዳ መሆኑ በሚኒስትር መ/ቤቱ ከተከናወነው በአቢሲኒያ ካርድና በካሽ ኩፖን የነዳጅ አጠቃቀም የውስጥ ኦዲት ሪፖርት የተገለጸ ሲሆን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን ተገንዝበናል፣

69. እንዲሁም በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሰሌዳ ቁጥር 4-01910 በ03/01/03 80 ሊትር/40X2/፣ 4-02199 በ08/09/04 100 ሊትር በቀን ሁለት ጊዜ ከተማ ውስጥ መቅዳታቸው ታውቆ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን፣

70. በግብርና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአንድ ሳምንት ውስጥ ለበላይ ኃላፊዎች የተወሰነ ኮታ 30 ሊትር እና ለጋራ አገልግሎት 40 ሊትር እንደተፈቀደ መረጃዎች ያመለክታሉ፣ ሆኖም ለሰሌዳ ቁጥር 4-14079 ከ02/01/04-29/01/04 በ26 ቀናት ውስጥ 510 ሊትር ወይም በ1 ሳምንት 127.5 ሊትር እና በ14 ቀናት ከ02/09/04-15/09/04 ውስጥ ለሰሌዳ ቁጥር 4-00617 150 ሊትር ወይም በ1 ሳምንት 75 ሊትር ያለ ኮታ ከተማ ውስጥ ነዳጅ እንደተቀዳላቸው ከስምሪት ቅጽ ለማወቅ ተችሏል፡፡ነገር ግን ሚኒስትር መ/ቤቱ ካለው የኮታ አሰራር አንጻር የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ አለመኖሩን ተረድተናል፡፡

71. በኢትየጵያ መንገዶች ኮርፖሬሽን ደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት ለትላልቅ ተሽከርካሪዎች 1.43 ኪሎ ሜትር በሊትር ለትናንሽ ደግሞ 5.88 ኪሎ ሜትር በሊትር ተብሎ የተቀመጠ ቢሆንም፣ ERA no 50270 ቶዮታ (Toyota) ትንሽ ተሽከርካሪ የተቀመጠለት ልኬት በሊትር 5.88 ኪ.ሜ ሲሆን 3.79 ኪ.ሜ በመጓዙ በሊትር 2.09 ኪ.ሜ ከልኬት በታች የተጓዘ መሆኑ፣ እንዲሁም ERA no 58201 Terano Nissan የተቀመጠለት ልኬት በሊትር 5.88 ኪ.ሜ ሲሆን በሊትር 4.40 ኪ.ሜ የተጓዘ በመሆኑ ከተቀመጠለት ልኬት በልዩነት የ1.48ኪ.ሜ. የተጓዘ መሆኑን ከዲስትሪክቱ የጥቅምት ወር ወርሃዊ የተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. ስለ ሁኔታው በናሙና የተመረጡ እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አዲስ በመሆናቸው ስለጉዳዩ የማያውቁ መሆኑን እና በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ በጊዜው እንዳልነበሩ የገለጹ ሲሆን፣ እንዲሁም በጤና ጥበቃ ሚ/ር ሁኔታው የተፈጸመው ከሶስት ዓመት በፊት መሆኑን ገልጸው በወቅቱ በውስጥ ኦዲት በኩል አስተያየት የተሰጠበት መሆኑን ቢገለጽም ስለተጠሰው አስተያየት የሚገልጽ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ሊያቀርቡልን አልቻሉም፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የተሰጠው መልስ ተሽከርካሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ የሚቀዱበት አጋጣሚ ሊኖር አይችልም የሚል ነው፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽ ደብረማርቆስ ዲስትሪክት ከተቀመጠላቸው ልኬት በታች ወርደው ከ1.48 ኪሎ ሜትር እስከ 2.09 ኪሎ ሜትር በሊትር መጠቀማቸውን በተመለከተ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ሪፖርቱን ያቀረቡት ሾፌር እንዲጠየቁ ተደርጎ ምክንያቱን እንደገለጹት ሪፖርት ያልተደረገ የጉዞ ኪ.ሜ.መኖሩን ተረጋግጦ የትምህርት ደረጃቸው ዝቅተኛ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ከዚህ በኋላ ለሚቀርብ ሪፖርት የቅርብ አሰሪዎቻቸው ክትትል እንዲያደርጉ የተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

73. የነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥርን አስመልክቶ ችግሮችን በመለየት እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ የተጠያቂነት ሥርዓት እንዳይኖር በማድረግ ለወደፊት የነዳጅ ብክነት እንዲስፋፋ መንገድ የሚከፍት አሰራር እንዲኖር ያደርጋል፡፡

<u>የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ወጥ /standardized / እና ወቅታዊ የሆነ መመሪያ መኖሩን፣ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች መዘጋጀታቸውን እና ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን በተመለከተ፤</u>

74. በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ተሽርካሪዎች ወጥ /standardized/ እና ወቅታዊ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ ሊያዘጋጅ፤ የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ስልጠና በመስጠት የሰለጠነ እና ልምድ ያለው ባለሙያ እንዲኖር ሊያደርግ እና በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት

ያላቸው ሰነዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ወቅታዊ እንዲደረጉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

75. ሆኖም በኤጀንሲው የተሽከርካሪ ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ላይ ነዳጅን በተመለከተ ጥቂት መመሪያ ያለ ቢሆንም የነዳጅ አጠቃቀም ዝርዝር መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ እና ነዳጅ እንደ ማንኛውም እስቶክ በማየት የሚታለፍ እንጂ ለብቻ ተነጥሎ ስልጠና እንደማይሰጥ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

76. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር፣ በግብርና ሚ/ር፣ በጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ በግብርና ምርምር ኢንሲቲትዩት፣ በማዕከላዊ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ በማዕድን ሚ/ር፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በባህር ዳር እስታትስቲክስ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እና በኢትዮጵያ መንገዶች ኮርፖሬሽን በደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት) በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ወጥ በሆነ መንገድ ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑን እና በተሽከርካሪ ስምሪት ላይ የሚመደቡ ባለሙያዎች ሙሉ በሙሉ በነዳጅ አጠቃቀም ቁጥጥር ላይ በቂ ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያስችል ስልጠና ያልወሰዱ መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

77. የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ነዳጅ፣ በአላቂ ንብረትነት የሚታወቅ መሆኑን እና በአለቂ ንብረቶች የአሰራር ማንዋል ቅጾችን ጨምሮ በአጠቃላይ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ነዳጅ እንደ እስቶክ በማየት የሚታለፍ እንጂ ለብቻ ተነጥሎ ስልጠና ያልተሰጠ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

78. በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ተሽርካሪዎች ወጥ /standardized/ እና ወቅታዊ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ ሊዘጋጅ፤ የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ስልጠና በመስጠት የሰለጠነ እና ልምድ ያለው ባለሙያ እንዲኖር ሊያደርግ እና በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እንዲሁም ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች /ቅጾች/ ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ወቅታዊ እና ወጥ እንደሆኑ አለማድረግ ለአሠራር እና ለቁጥጥር አመቺ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓት እንዳይኖር በማድረግ ነዳጅን አለአግባብ ለመጠቀም በር ሊከፍት ይችላል፡፡

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን በተመለከተ፤

79. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት በዚሁ መሠረት የክትትልና ግምገማ ሥራ ሊከናወን ይገባል፡፡

80. በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ያሉ ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ በዓይነትና የሚገኙበት መ/ቤት በመረጃ አለመያዛቸው እና ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ እስከ አሁን የተደረገ ኦዲት አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡

81. የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የተሽከርካሪዎቹን ብዛት የሚገልጽ መረጃ በየመ/ቤቶቹ ሊገኝ እንደሚገባው እና ነዳጅ ተለይቶ ሳይሆን በእስቶክ ውስጥ እንደሚታይ ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ነዳጅ በስቶክ ውስጥ ቢታይም ካለው የተለየ ባህሪ አንጻር የተለየ ኦዲት ሊደረግና በግድፈቶችና ችግሮች በመለየት የማስተካከያ እርምጃ የአጠቃቀምና የአሠራር ማሻሻያ ሥርዓት ሊደረግ ይገባል፡፡

82. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን አለመዘርጋት በመንግስት መ/ቤቶች ተጠያቂነት እንዳይኖር በማድረግ ነዳጅ ለታለመለት ተግባር እንዳይውል ያደርጋል፡፡

ክፍል ሦስት

የመደምደሚያ ሀሣቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እንደተመለከተው በፌዴራል መንግስት መ/ቤት ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የግዥና ንብረት ክንውን፣ክትትልና ሪፖርት የማድረግና የማረጋገጥ ኃላፊነት የተሰጠው ኤጀንሲውና በናሙና ለኦዲት ተመርጠው በታዩት የፌዴራል መ/ቤቶች የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ተሰጥተዋል፦

83. የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በ2001 በጀት ዓመት የተቋቋመና የተሽከርካሪ አጠቃቀም ስምሪት መመሪያም እስከ 2004 በጀት ዓመት ድረስ ያልወጣ መሆኑ እና በ1977 ዓ.ም. የወጣውም መመሪያ በአስፈጻሚ መ/ቤቶች በተሟላ ሁኔታ የማይታወቅ እና ባለቤት ያልነበረው በመሆኑ በዚሁ መሠረት ወጥ እና ለቁጥጥር አመቺ የሆነ ሥርዓት አሠራር በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ባለመኖሩ የነዳጅ አጠቃቀምን ተጠያቂነት በሰፈነበት አግባብ ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ሳይዘረጋ የነበረ መሆኑ፣

84. ኤጀንሲው የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የቋሚ እቃ እና አላቂ እቃ ማንዋል ያዘጋጀ እና በእነዚህ ላይ ስለ አሠራሩ ለአስፈጻሚዎችም ስልጠና የሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡ሆኖም ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ የሚፈስበትን ነዳጅ ለመቆጣጠር የሚያስችል ብቁ የሆነ ባለሙያ ለማፍራት እንዲቻል እያንዳንዱ አስፈጻሚ በሥሩ ላሉ በአሽርካሪነት ዘርፍ ለተሠማሩ ሠራተኞች ሥልጠና መስጠት ሲገባቸው ሥልጠና ያልተሠጡ መሆኑ ፣ አጀንሲውም ነዳጅን ከፍተኛ ስጋት(Risk) ያለበትን እንደ ሌሎች ማንኛውም አላቂ ዕቃዎች (እስቶክ) በመቁጠር ጥቅል ሥልጠና የሰጠና ለብቻ ተነጥሎ በመንግስት መ/ቤቶች ለነዳጅ ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጥ ስልጠና ያልሰጠ እና እንዲሰጥም ያልተመቻቸ መሆኑ፣

85. የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት መ/ቤቶች የተጠያቂነት ስርዓት እንዲኖር ለማድረግ ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ኦዲት ማድረግ ሲጠበቅበት፣ እስከ 2004 በጀት ዓመት ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ኦዲት ያላከናወነ መሆኑ፣

86. ነዳጅን ለመቆጣጠር እና በነዳጅ ዙሪያ አጥጋቢ መረጃን ለመያዝ በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ መዋል እና ወቅታዊ ሊደረጉ ሲገባቸው፣ በኤጀንሲው ነዳጅን በአላቂ ንብረትነት ከማየት ውጪ ለብቻው ትኩረት ሰጥቶት በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶችን ወጥ በሆነ መንገድ አዘጋጅቶ በመንግሥት መ/ቤቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ፣

87. በአብዛኛው በናሙና በታዩት የፌዴራል መንግስት ተቋማት ነዳጅን በአግባቡ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል ጥናት ተጠንቶ ተግባራዊ መደረግ ሲገባው አለመጠናቱ እንዲሁም የበላይ ኃላፊዎች ለነዳጅ አጠቃቀም ትኩረት በመስጠት በሪፖርት የመቆጣጠር ሥራ፣ ሥልጠና እንዲሰጥ የማድረግ እና ጥናት እንዲካሄድ የማድረግ ሥራ አለመከናወኑ፣

88. የመንግሥትና ህዝባዊ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ግዥ ሥምሪት አጠቃቀምና ጥገና መመሪያ ያለ ቢሆንም መመሪያውን ወቅታዊ በማድረግ የተሽከርካሪ ጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት በኤጀንሲው እስከ 2004 ዓ.ም. ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ፤

89. በኦዲቱ በታዩ አስር (10) መ/ቤቶች በአምስቱ (5) ከ2002 በጀት ዓመት እስከ 2003 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የተመደበው በጀት ከአፈጻጸሙ ጋር ልዩነት ያለው መሆኑ፣ አራቱ የተመደበላቸውን በጀት 15% እና ከዚያ በላይ ያልተጠቀሙ ሲሆን ፣በአንዱ ከተያዘለት በጀት ከ (7.68%) በላይ የተጠቀመ መሆኑ፣

90. በኦዲቱ በታዩ 8 መ/ቤቶች በጋራ አገልግሎት ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙ ሰራተኞችን አቀናጅተው ማሰማራት ሲኖርባቸው፣ በጋራ ተቀናጅተው ስለተጓዙ ሰራተኞች መረጃ ማቅረብ አለመቻሉ፣

91. በናሙና በታዩት መ/ቤቶች በ8ቱ እንደ ስራው ፀባይ እና ተሽከርካሪው አይነትን መሠረት በማድረግ ነዳጅን ለመቆጣጠር የሚያስችል በሳምንትም ሆነ በወር ለአንድ ተሽከርካሪ የሚያስፈልገው የነዳጅ መጠን ሊታወቅ እና ኮታ ሊቀመጥለት ሲገባው፣ ለአንድ ተሽከርካሪ ያለገደብ ነዳጅ የሚቀዳ መሆኑ ፣

92. ለመንግስት የበላይ ኃላፊዎች በወር የተመደበ የነዳጅ መጠን ናፍጣ እስከ 165 ሊትር እና ቤንዚን 135 ሊትር ሲሆን ነገር ግን በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በወር ለፕሬዝዳንቱ እስከ 450 ሊትር እና ለምክትል ፕሬዝዳንቱ እሰከ 300 ሊትር ነዳጅ የተቀዳለት መሆኑ፣

93. በናሙና በታዩት በአስራ አንዱ (11) መ/ቤቶች የነዳጅ ፍጆታን የተለያየ ቅጽ ላይ ቢመዘግቡም ወጥ በሆነና ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ነዳጅ ሲቀዳ የኪሎ ሜትር ንባብ፣ ተሽከርካሪው ለሥራ ሲሰማራ የሄደበት እና የሚመለስበት ሰዓት በተዘጋጁ ቅጾች ላይ የማይመዘግቡ መሆኑ፣

94. በኦዲቱ በናሙና ከታዩ 11 መ/ቤቶች በ7ቱ፣ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነትና በሞዴል ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል የሚገልጽ ሰነድ አለማዘጋጀታቸው፣ ነገር ግን በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እና በማዕድን ሚ/ር ከዚህ በፊት የተዘጋጀ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉ፣

95. በሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች የተሽከርካሪው ኪ/ሜትር ቆጣሪው የሚሠራ መሆኑ ተለይቶ መታወቅ ሲገባው በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር 4-01922፣ 4-02769፣ 4-01921፣ 4-02768፣ 4-00720፣ 4-01750፣ 4-01924፣ 4-01917 ከስምሪት ክፍል በተገኘው መረጃ ጌጃቸው የሚሰራ መሆኑ ሲገለጽ፤ ነገር ግን በ2002 ዓ.ም በነዳጅና ቅባት መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ ለማየት መቻሉ፣

96. በኦዲቱ ወቅት በታዩ 10 መ/ቤቶች፣ ጌጃቸው ለማይሰሩ ተሽከርካሪዎች የመቆጣጠሪያ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣

97. በኦዲቱ ወቅት በታዩ 8 መ/ቤቶች፣ በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

98. በናሙና በታዩ 8 መ/ቤቶች ከኮታ በላይ ሲጠቀሙ በነበሩ እና እንዲሁም በመንገዶች ኮርፖሬሽን ደብረማርቆስ ዲስትሪክት ከወጣላቸው ልኬት በታች ያሽከረከሩ አሽከርካሪዎችን በመለየት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

99. በአጠቃላይ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ያለውን ሁኔታ ለማሻሻል የተሸከርካሪ ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 በ2004 በ.ዓ. መጨረሻ ላይ የወጣ ቢሆንም፣ ከዚያ በፊት በናሙና በተመረጡ መ/ቤቶች የነበረው የነዳጅ አጠቃቀም ወጥ ያልሆነ፣ያልተሟላ እና ለብክነት የሚዳርግ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ኤጀንሲው ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ከመሆኑ አንጻር እና የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ስርዓት በአግባቡ ባለመዘርጋቱ የነበረው የአሰራር ሥርዓት በ1977 ዓ.ም. የወጣ በመሆኑ እና የቆየ በመሆኑ ፣ለነዳጅን አጠቃቀም እና ቁጥጥር ተገቢውን ትኩረት ባለመደረጉ ተጠያቂነት በሰፈነበት አግባብ ለመፈጸም እና ለመከታተል ሳያስችል ቀርቷል፡፡

100. ስለሆነም የመንግስት መ/ቤቶች የተሸከርካሪ ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ላይ ነዳጅን በሚመለከት በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ተገቢውን ተጨማሪ የቁጥጥር እና የአሠራር ሥርዓቶች አክለውበት የማይጠቀሙ ፣ እንዲሁም ኤጀንሲው ወጥ እና ወቅታዊ ለመሆኑ እና በዚያ መሠረት ተግባራዊ ለመደረጉ ተገቢውን ክትትል በማድረግ የሚታዩ ድክመቶችን በየጊዜው በመከታተል ተጨማሪ ዝርዝር መመሪያና የማስተካከያ እርምጃ የማይወስድ ከሆነ ከፍተኛ ሃብት የሚፈስበትን ነዳጅ በብቃት፣ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደርጋል፡፡ እንዲሁም የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር በኤጀንሲው የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ኦዲት ካልተደረገ ነዳጅ ያለአግባብ ጥቅም ላይ እንዲውል ክፍተት ይፈጥራል፡፡ ስለሆነም ከላይ የተገለጹት ድክመቶችና ግድፈቶች በነዳጅ አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድሩ፤ በብቃት፣ ኢኮኖሚ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓታቸውን ጠብቀው እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

ክፍል አራት

<u>የማሻሻያ ሀሣቦች</u>

101. በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለሁሉም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት ተሽከርካሪዎች በዝርዝር ጥናት ላይ የተመሠረተ፣ ወጥ እና ወቅታዊ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ በማዘጋጀት ነዳጅን ለመቆጣጠር እና ተጠያቂነት በሰፈነበት አግባብ ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

102. የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ የፌዴራል መንግስት መ/ቤት ኃላፊዎች በአሽከርካሪ ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ ሠራተኞች ስልጠና እንዲሰጥ በማድረግ ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ የሚፈስበትን ነዳጅ ለመቆጣጠር የሚያስችል ብቁ የሆነ ባለሙያ ማፍራት ይገባል፡፡

103. በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት መ/ቤቶች ተጠያቂነት እንዲኖር ከነዳጅ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ኦዲት በማከናወን የክትትልና ግምገማ ስርዓቱን ማጠናከር ይገባል፡፡

104. ነዳጅን ለመቆጣጠር እና በነዳጅ ዙሪያ አጥጋቢ መረጃን ለመያዝ በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ መዋል እና በየጊዜው በማሻሻል ወቅታዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

105. ማንኛውም የፌደራል መንግስት መ/ቤት እንደየሥራው ባህሪይ የተመደበውን የነዳጅ በጀት ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል የነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር ጥናት ሊያካሂድ ይገባል፡፡

106. የፌደራል ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ትኩረት በመስጠት ሥልጠና እንዲሰጥ፣ ጥናት እንዲካሄድ እና ሪፖርት እንዲቀርብላቸው ሊያደርጉ ይገባል፡፡

107. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ነዳጅን እንዲጠቀሙ የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

108. ለመንግስት መ/ቤቶች የሚመደበውን ነዳጅ በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ በጋራ አገልግሎት (Pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን

በተመለከተ የየሥራ ክፍሎችን የተሽከርካሪ ጥያቄዎች በማገናዘብ እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ ለሥራ የሚጓዙትን የመ/ቤቱ ሠራተኞች በማቀናጀት በጋራ ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

109. የፌደራል መንግስት ተሽከርካሪ የነዳጅ አጠቃቀም የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚያስችል በጥናት ላይ የተመሰረተ ለአንድ ተሽከርካሪ በወርም ሆነ በሳምንት የተወሰነ ኮታ ሊመደብለት ይገባል፡፡

110. ለመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች እና ለዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንቶች ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታን የከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ መሠረት ሊሆን ይገባል፡፡

111. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ለቁጥጥር እና ክትትል ያመች ዘንድ ወጥ የሆነ የነዳጅ፣ የዘይት እና የቅባት መመዝገቢያ ቅጽ ሊኖር እና ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡

112. ለመንግስት መ/ቤቶች የሚመደበውን ነዳጅ ለመቆጣጠር እና ለመከታተል ያስችል ዘንድ ለአንድ ተሽከርካሪ ነዳጅ መቀዳት ያለበት በተወሰነለት ኮታ መሰረት ነዳጅ የሚያስፈልገው የሥራ ክፍል ኃላፊ በተሞላ የነዳጅ ቅጽ ላይ ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ መሆን አለበት፡፡

113. የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተልና መዝግቦ ለመያዝ እንዲረዳቸው ነዳጅ በሚሞላበትና የነዳጅ ኩፖን በሚሰጥበት ወቅት የተሽከርካሪው የኪሎሜትር ንባብና የሚሞላው የነዳጅ መጠን በቅጽ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡

114. ነዳጅን ለመቆጣጠር እና በአግባቡ ለታለመለት ሥራ እንዲውል እያንዳንዱን ተሽከርካሪ በአይነትና በሞዴል ተለይቶ በአንድ ሊትር ነዳጅ በአማካይ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል ሊታወቅ እና በዚሁ መሠረት ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

115. በናሙና በተመረጡ በሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች በአስራ አንዱ (11) ዕለታዊ የተሽከርካሪ ስምሪት ቅጽ ተዘጋጅቶ በአግባቡ እየተሞላ ተሽከርካሪው የሄደበት እና የሚመለስበትን ሰዓት በመቆጣጠር ተሽከርካሪው ከመንግስት ሥራ ውጭ የሚደረጉ ጉዞዎችን በማስቀረት ለነዳጅ ቁጥጥሩ እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡

116. ነዳጅን ለመቆጣጠር እና ከብክነት ለመታደግ ይቻል ዘንድ የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የኪ/ሜትር መመዝገቢያ ቅጽ በተሟላ መልኩ ተመዝግቦ በመረጃነት ሊያዝ ይገባል፡፡

117. እያንዳንዱን ተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታ በመለካት ከመ/ቤቱ የሥራ ስፋት ጋር በማነጻጸር ለነዳጅ የሚታቀደው በጀት በጥናት ላይ የተመሰረተ እና አፈጻጸሙም ከዕቅዱ ጋር የሚጣጣም ሊሆን ይገባል፡፡

118. የፌደራል መንግስት መ/ቤት ተሽከርካሪ በኪሎ ሜትር የነዳጅ ፍጆታቸውን ለማወቅ እና ለመቆጣጠር የተሽከርካሪው ኪ/ሜትር ቆጣሪው /ጌጁ/ የሚሠራ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

119. የመንግሥት መ/ቤት ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው በሚበላሽበት ወቅት በአፋጣኝ ጌጃቸው ሊጠገን ወይም ሊቀየር ይገባል፡፡ የቆዩ እና መለዋወጫ የማይገኝላቸው ተሽከርካሪዎች በታንከራቸው ላይ የሽቦ ወንፊት በማሰራት ሊገለገሉባቸው ይገባል፡፡በሊትር ሊሄዱ የሚችሉበት ኪሎ ሜትር ርቀትም በጥናት ሊወሰን ይገባል፡፡

120. በነዳጅ ላይ የቁጥጥር፣ የክትትል እና የተጠያቂነት ስርዓትን ለመዘርጋት እንዲያስችል ተሽከርካሪው የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር መጠን ጋር እና ከተከናወነው ሥራ ጋር በመመዝገብ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

121. የመንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ወርሃዊ የነዳጅ የዘይትና የጥገና ወጪ ተለይቶ ወጥ በሆነና ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ በሪፖርት መልክ ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ በላይ ኃላፊ ሊቀርብ ይገባል፡፡

122. ነዳጅን በአግባቡ ለመጠቀም እና ለመቆጣጠር የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት በአሠራር ላይ የተከሠቱ ችግሮችን ለይቶ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

123. እያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት በሥሩ ላሉት ተሽከርካሪዎች ያወጣውን የነዳጅ፣ የዘይት፣ የጥገና ወጪ ቅጽ መተአ 015 በመሙላት በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ለሚመለከተው ለየመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም የኤጀንሲውና በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ የታዩ መ/ቤት ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት የሚፈለጉ መረጃዎችን እና ለኦዲቱ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በሙሉ በማቅረብ እንዲሁም ለቀረቡ ቃለ-መጠይቆች በወቅቱ መልስ በመስጠት ለተደረገልን ትብብር ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

የአሠራር መግለጫና ሚና (process description and roles)

- **ስቶክ ማኔጅመንት ስርዓትስቶክ መቀበልና መፈተሽ**

  ስቶክ መቀበል ማለት ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ ንብረቶችን ቆጥሮ፣ ለክቶና ፈትሾ የመረከብ ሂደት ነው፡፡ የግዥ፣ ስጦታና በሌላ ማንኛውም መንገድ የሚገኙ ዕቃዎች የጥራት ችግር፣ የመጠን ዕጥረትና ብልሽት ሊታወቅ የሚችለው ትክክለኛ የአቀባበልና የፍተሻ ተግባር ሲከናወን ነው፡፡

- **ስቶክ የመቀበል ኃላፊነት**

  የዕቃ ግ/ቤት ኃላፊ ከማንኛውም ምንጭ የሚገኝ ዕቃን ፈትሾ መረከብ ይኖርበታል፡፡ ለመ/ቤቱ የግዥ ክፍል ከሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ የተፈፀሙ ግዥዎች የዕቃ ዝርዝር /ስፔሲፊኬሽን/ ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

- **ቅጾች**
  - የዕቃ ወይም የንብረት ገቢ ደረሠኝ /ሞዴል 19/
  - የዕቃ ጉድለት ወይም እጥረት ሪፖርት ናቸው

- **ስቶክ የመቀበል ሥርዓት**

  ስቶክን ከማንኛውም ምንጭ ተረክቦ ሥራ ላይ ከማዋል በፊት የሚከተሉትን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

  - ንብረት ከማንኛውም ምንጭ ለማግኘት ኃላፊነት የተሠጠው ኃላፊ ስቶክ እንዲገባ ፈቃድ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ይህም በጽሑፍ ቢሆን ይመረጣል፡፡
  - እቃውን ለመቀበልና ርክክብ ለመፈፀም የሚገባው ቦታ በቅድሚያ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ በአብዛኛው ይህ ቦታ የዕቃ ግ/ቤት ሲሆን ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች የሥራ ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡
  - የመቀበልና ርክክብ ሥነ-ሥርዓቱ በሙሉ ከመፈፀሙ በፊት ዕቃውን ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ አይሆንም፡፡

- **ስቶክ ወጪ ማድረግ**

  ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች ከዕቃ ግ/ቤት አገልግሎት ማግኘት የሚጀምሩት የዕቃ ግ/ቤት ኃላፊ ስቶክ ወጪ ማድረግ ሲጀምር ነው፡፡

  ስቶክ ወጪ ማድረግ በሁለት ይከፈላል፡- የመጀመሪያ ዕቃዎች በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ለሚገኙ የሥራ ክፍሎች ወጪ ማድረግ ነው፡፡ ሌላው ዕቃዎችን ከመ/ቤቱ ውጭ ለሚገኙ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ወይም ለሌላ አካላት ወጪ ሲደረግ ይሆናል፡፡

  በዕቃ ግ/ቤት የሚገኙ ስቶኮች የመ/ቤቱን ገንዘብ የያዙ በመሆኑ እንዳይጠፋ፣ እንዳይሰረቁና ለአላስፈላጊ ጉዳይ እንዳይውሉ ጥንቃቄና ስርዓት ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ከአሠራር አንፃር ስቶኮች ወጪ ሲደረጉ መስሪያ ቤቶች የሚከተሉትን አሠራር መከተል አለባቸው፡፡

- **ስቶክ ወጪ የማድረግ ኃላፊነት**

  ስቶክ ወጪ በማድረግ ሂደት የሚከተሉት ሶስት አካላት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የንብረት አስተዳደር ኃላፊው አጠቃላይ የዕቃ አወጣጥ ሥርዓት ስለመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

  የተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች ከዕቃ ግ/ቤት ወጪ ያደረጋቸውን ስቶኮች ለሚያከናውኗቸው ተግባራት አስፈላጊ መሆናቸውንና ለዚሁ ተግባር ብቻ ጥቅም ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
  የዕቃ ግ/ቤት ኃላፊ ዕቃዎች በሚመለከታቸው ኃላፊ የተጠየቀና ለዚህ ተግባር የተዘጋጁ ቅጾች በሚመለከታቸው ኃላፊዎች መፈረማቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

- **ቅጾች**
  - የዕቃ መጠይቅ /ሞዴል 20/
  - የዕቃ ወይም ንብረት ወጪ ደረሠኝ /መዴል 22/
  - የበር መውጫ ቅጽ /GP/

- **በመ/ቤቶች ስቶክ ወጪ የማድረግ አሠራር**

  ስቶክ ለተጠቃሚ ወጪ የማድረግ ሂደት የሚከተሉትን ሶስት ደረጃዎችን ያካትታል፡፡

ሀ. የዕቃ መጠይቁን ማፅደቅ፡-

ዕቃ ወጪ ከመደረጉ በፊት ዕቃ ወጪ ለማድረግ ሥልጣን የተሰጠው ኃላፊ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ የዕቃ ግ/ቤት ኃላፊዎችና የዕቃ ግ/ቤት ምዝገባ ሠራተኞች ዕቃ ወጪ ለማድረግና ለማፅደቅ ሥልጣን የተሰጣቸውን በመሥሪያ ቤቱ የሚገኙ ኃላፊዎችን ማንነት የሚገልጹ መዝገብ መያዝ አለባቸው፡፡ በዚህ መዝገብ ውስጥ የኃላፊዎቹን ሥም፣ የሥራ ድርሻ የፊርማ ናሙና መያዝ ይኖርበታል፡፡

ለ. የዕቃ መጠይቁን ማዘጋጀት፡-

የተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች የዕቃ መጠይቅ /ሞዴል 20/ በመሙላት የዕቃ ወጪ ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ የዕቃ መጠይቅ በተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች በአንድ ኮፒ ተዘጋጅቶና ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ ተፈርሞ እንዲፀድቅ ለንብረት አስተዳደር ኦፊሰር ይላካል፡፡

በንብረት አስተዳደር ኦፊሰር/የሥራ ሂደት ባለቤት የፀደቀ የዕቃ መጠይቅን መሠረት በማድረግ የዕቃ ግ/ቤት ኃላፊው የዕቃ ወይም ንብረት ወጪ ማድረጊያ ቅጽ /ሞዴል 22/ በ3 ኮፒ ያዘጋጃል፤

1. የመጀመሪያው ኮፒ ከዕቃ መጠይቁ ጋር በማያያዝ ለዕቃ ግ/ቤት ምዝገባ ሠራተኛ ይላካል፡፡ ይህንን ሰነድ መሠረት በማድረግ የዕቃ ግ/ቤት ምዝገባ ሠራተኛው የስቶክ ሪከርዱን ይሞላል፡፡
2. ሁለተኛው ኮፒ ለጠያቂው የሥራ ክፍል ይላካል፡፡ ይህም ለጠያቂው የሥራ ክፍል ማስረጃና ወደፊት ዕቃ ሊጠይቅ የተጠቀመበትን ለመግለጽ ያገለግላል፡፡
3. ሶስተኛ ኮፒ ለዕቃ ግ/ቤት ኃላፊው ማስረጃ ሆኖ እንዲያገለግል ይቀመጣል፡፡፡

- የተጠየቀው ዕቃ ለተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች ርክክብ መፈፀም፣

ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች የጠየቋቸውንና የተፈቀደላቸውን ዕቃዎች ቆጥረውና ለክተው መረከብ ይኖርባቸዋል፡፡

አባሪ -2

<u>የኦዲት መመዝገኛ መስፈርቶች</u>

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት የኦዲት መስፈርት (Evaluative Criteria)
1. ማንኛውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት ለተሽከርካሪዎች ስምሪት የሚያስፈልገውን የነዳጅ በጀት መጠን በዕቅድ የያዘውን የመንግሥትን ሥራ ለማስፈጸም በሚያስችል ጥናት ላይ የተመሠረተ ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ መደረጉን ማጣራት፡፡	1. ስለ መንግሥት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደር ጥናት ሊካሄድ ይገባል፡፡ 2. የነዳጅ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ለነዳጅ ግዥና አስተዳደር ሥራ ተገቢውን ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡ 3. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ነዳጅን እንዲጠቀሙ የጥገናና የእንክብካቤ ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ 4. የአንድ ተሽከርካሪ ግዥ ጥያቄ ሲቀርብ የነዳጅ፣ ቅባት እና ጥገና ወጪ አንድምታ አብሮ ሊታይ ይገባል፡፡
2. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ማጣራት፣	5. ማንኛውም የመንግሥት ተሽከርካሪ ለተመደበለት ሥራ ካልሆነ በስተቀር ሊንቀሳቀስ ወይም ለግል መጠቀሚያ ሊውል አይችልም፡፡ 6. በጋራ አገልግሎት (pool) ሥር የሚገኙ ተሽከርከሪዎችን በተመለከተ የየሥራ ክፍሎችን የተሽከርካሪ ጥያቄዎች በማገናዘብ እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙትን የመ/ቤቱ ሠራተኞች በማቀናጀት ለሥራ በጋራ ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ 7. ለመንግሥት ተሽከርካሪ የሚሰጥ የነዳጅ ዕደላ ከሥራው ጠባይና ሁኔታ አንጻር ተገምግሞ በኮታ መወሰን አለበት፡፡

	8. ለመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች የተሽከርካሪ የነዳጅ ፍጆታ የከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችን ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት መመሪያ መሠረት ሊሆን ይገባል፡፡
	9. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ወጥ የነዳጅ፣ ዘይት እና ቅባት መመዝገቢያ ቅጽ ሊኖር ይገባል፡፡
	10.ለአንድ ተሽከርካሪ ነዳጅ መሞላት ያለበት በተወሰነለት ኮታ መሠረት የነዳጅ ቅጽ ፈቃድ ከተሞላ በኋላ መሆን አለበት፡፡
	11. ነዳጅ በሚሞላበትና የነዳጅ ኩፖን በሚሰጥበት ወቅት የተሽከርካሪው የኪሎሜትር ንባብና የሚሞላው የነዳጅ መጠን በቅጽ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡
	12. እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል መታወቅ አለበት፡፡
	13. በሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች ዕለታዊ የተሽከርካሪ ስምሪት ቅጽ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
	14. የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የኪ/ሜትር መመዝገቢያ ቅጽ መሞላት አለበት፡፡
	15. በፌዴራል መንግሥት ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተመደበው የነዳጅ በጀት ከአፈፃፀሙ ጋር ሊጣጣም ይገባል፡፡
	16. የተሽከርካሪው ኪ/ሜር ቆጣሪው የሚሠራ መሆኑን መረጋገጥ አለበት፡፡
	17. ጌጃቸው ለማይሠሩ የመንግሥት መ/ቤት ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
	18. በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	19. የመንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ወርሃዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የጥገና ወጪ ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል፡፡

	20. የነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥርን አስመልክቶ ችግሮችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
	21. በሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ ሥምሪት ክፍል ተግባርና ኃላፊነት በጽሑፍ በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል፡፡
	22. እያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት በሥሩ ላሉት ተሽከርካሪዎች ያወጣውን የነዳጅ፣ የዘይትና የጥገና ወጪ ቅጽ መተአ 015 በመሙላት በየሩብ ዓመቱ ለመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡
3. የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን የግዥና ንብረት አስተዳደር /ነዳጅን/ ክንውንና ክትትል በማድረግ ለገ/ኢ/ል/ ሚኒስትሩ ማቅረቡን እና ኦዲት ማድረጉን ማጣራት	23. ኤጀንሲው ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ወጥ (Standardized) እና ወቅታዊ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡
	24. የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡
	25. በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
	26. በነዳጅ አጠቃቀም ቁጥጥር ሥርዓት የሰለጠነ እና ልምድ ያለው ባለሙያ ሊኖር ይገባል፡፡
	27. በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾች እና ለነዳጅ አስተዳደር አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ መዋል እና ወቅታዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡